# “ውሸትና ስንቅ እያደረ ይቀላል”!!!

ከባህልቢ ዘማርያም

<u>ክፍል አራት</u>፤

የዚህ ፅሑፍ ክፍል ሶስት የሄግ ውሳኔን አስመልክቶ ሐጎስ ዮሐንስ ያሰፈሩት የተዛባ አመለካከትን በመተቸት ነበር የተቋጨው። የዛሬ ደግሞ በፅሑፋቸው ውስጥ ሁለተኛ ፓረግራፍ ላይ እንደሚከተለው የሰፈረውን በመተቸት ይጀምራል።

> “……… *በተመሳሳይም የአፍሪቃ ቀንድ መሪዎች፤ መንግሥታትና ህዝብ፤ ስለአፍሪቃ ቀንድ ታሪክና ጥንታዊ ሥልጣኔ፤ ፖለቲካና ኢኮኖሚን ለመቆጣጠር ያለው ስትራቴጂዊ ጠቀሜታ አስፈላጊ እውቀትና ግንዛቤ ያጥራቸዋል።በሌላ አባባል፤ ተራ አፍሪቃዊ ያልሆነ ነጋዴ፣ እንበል፡ ኤውሮጳዊ ወይም አሜሪካዊ የአፍሪቃ ቀንድ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ጠቀሜታን ከአንድ የአካባቢው ፕሮፌሽናል የፖለቲካ ባለሙያ ከሚሊዮን ጊዜ በላይ የበለጠ ያውቃል ብል ማጋነን አይሆንም። በአመለካከቴ፤ ሁኔታው ለመላው አፍሪቃም ተመሳሳይ ነው።” የሚለው ይሆናል።*

ከላይ የሰፈረው የሓጎስ ዮሃንስ አባባል  ከተራ ስሜታዊ አነጋገር የዘለለ ይዘት አይታይበትም። ይህ ፀሐፊ አገላለጹን አይጋራም። ምክንያቱም የተሰነዘረው አመለካከት ሌጣ ነው፤ በምክንያትም አልተደገፈም። የአፍሪቃ ቀንድ መንግሥታትና መሪዎች የሚያውቋቸውና የሚገነዘቧቸው ሁኔታዎች የተሟሉ ላይሆኑ ይችላሉ። ጭራሽ ግንዛቤ ያጥራቸዋል ብሎ መደምደም ግን በራስ ላይ ያለው የግንዛቤ እጥረትን የሚያመላክት ይሆናል። አንዱ ከሌላው የተለየ አመለካከት ይኖረዋል። እያንዳንዱ ነገሮችን የሚያይበት የራሱ መነጽር አለው። ያ መነጽር ደግሞ እያንዳንዱ ለራሱ ካለው ስትራቴጂያዊ ግብ አንጻር ነው የሚያየው። ለምሳሌ አቶ መለስና የሻዓቢያው አቶ ኢሳያስ የአፍሪቃ ቀንድ ፖለቲካን የሚያዩት ከየራሳቸው ግብ አንጻር ነው። አያዩም ግንዛቤ ያጥራቸዋል ማለት ግን ስሕተት ነው ብሎ ያምናል ይህ ፀሐፊ። የአቶ መለስም ሆነ የአቶ ኢሳያስ ግንዛቤ ላይጥመንና ላንቀበለው እንችላለን። ግንዛቤ ያጥራቸዋል ብለን ለማስቀመጥ ግን አንችልም። ምናልባት ሐጎስ ዮሐንስ ለማለት የፈለጉትን ነገር ዘርዘር አድርገው ገልጸውት ቢሆን ኖሮ የምንጋራቸውም የምንለያይባቸውም አመለካከቶች ሊኖሩ ይችሉ ነበር። አሁን ባስቀመጡት መልኩ ሲታይ ግን ግርድፍ የማይሞላ ነው። ለነገሩ ከፅሑፋቸው ርእስ አንጻር ሲታይ እንዴትና በምን ምክንያት ወደዛ ነጥብ እንደገቡም ግልጽ አይደለም። የሆነ ሆኑ እዚህ የተነሳው ስላነሱት ብቻ በመሆኑ ብዙ ዝርዝር ውስጥ መግባቱ አስፈላጊ ባይሆንም፤ ካነሱት ዘንዳ በተወሰነ መልኩ አንዳንድ ነጥቦችን ነካክተን እንለፍ።

የአፍሪቃ ቀንድ ፖለቲካ፤ ታሪክ፤ ጥንታዊ ሥልጣኔና የአከባቢው ስትራቴጂያዊ ጥቅምን አስመልክቶ አንድ ተራ አሜሪካዊ ወይም ኤውሮጳዊ ነጋዴ ከአፍሪቃዊ ፕሮፌሽናል የፖለቲካ ባለሙያ የበለጠ እውቀት ወይም ግንዛቤ አለው ብሎ ለመናገርና ለመፃፍ መቻል ከይቅርታ ጋራ ድፍረት ወይም ስድብ ሆኖ ይሰማኛል። በርግጥ የተወሰኑ ምሁራን፤ ከሙያቸው አንጻር ባጀት ተመድቦላቸው ሰፊ ጥናት በማድረግ ያዳበሩት የአፍሪቃ ቀንድ ዜጋ እንደዜጋ ያልተገነዘባቸው እውቀቶችና ግንዛቤዎች የገበዩ ለመኖራቸው የሚያከራክር አይደለም። እነዚህም ቢሆኑ ኤውሮጳዊያን ወይም አሜሪካዊያን ብቻ አይደሉም። ባደረጉቸው ጥናቶች አንቱ የተባሉ ብዙ በስም ሊጠቀሱ የሚችሉ ኢትዮጵያዊያን ምሁራኖችም አሉ። የሌሎች የአፍሪቃ ቀንድ አገሮች

ሙሑራኖችም አሉ። ሆኖም፤ ከአንድ አገር ዜጎች በላይ ስለ አንድ ሀገር ታሪክ፤ ምጣኔ ሀብታዊ ይዘትም ሆነ ፖለቲካዊ ሂደት…. ወዘተ የበለጠ ጥናት በማድረግ የበለጠ እውቀት ያዳበሩ የኤውሮጳም ሆነ የአሜሪካ ምሁራን መኖራቸው የሚካድ አይሆንም። ይህ ደግሞ የአፍሪቃ ቀንድ ወይም የአፍሪቃ ብቻ ችግር አይደለም። የአሜሪካ ዜጋ ስለ አሜሪካ ሁሉም ነገር ያውቃል ለማለት እንደማይቻል ሁሉ የአፍሪቃ ቀንድ ዜጎችም ስለ አገራቸው ሁሉም ነገር ያውቃሉ ለማለት ባይቻልም አንድ ተራ አሜሪካዊ ወይም ኤውሮጳዊ ነጋዴ ከነሱ በላይ ስላገራቸው ያውቃል የሚለው ድንበሩን የዘለለ አባባል ይሆናል። ይህ ፀሐፊ እንኳ እንደአቅሚቲ! ስለአገሩ ከአንድ ተራ ኤውሮጳዊ ወይም አሜሪካዊ ነጋዴ በላይ ግንዛቤ አለኝ ብሎ ያስባል። ያለመታደል ሆኖ የአፊሪቃ ቀንድም ሆነ የአብዛኛው አፍሪቃ አገሮች በአምባገነን መሪዎች ምክንያት አጠቃላይ ጉስቁልና ውስጥ ተዘፍቀው ቢገኙም፤ አገራቸውን በሚመለከት ሊዛቅ የሚችል እውቀት ያላቸው ዜጎች መኖራቸውን መካድ የሚቻል አይሆንም። እዚህ ላይ ከሐጎስ ዮሐንስ ጋር የእውቀት መመዘኛ ልዩነት አለን። ይህ ፀሐፊ ባህላዊ እሴቱን የወረሰው ከወላጆቹና ካደገበት ህብረተ-ሰብ ነው። ያ ደግሞ አነሰም በዛ እውቀት ነው። የከባቢው የኗኗር ሁኔታ፤ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ይዘት፤ ፖለቲካዊ አስተዳደርና መሠረተ ልማታዊ እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት ከተራው ኤውሮጳዊ ወይም አሜሪካዊ ነጋዴ የበለጠ ግንዛቤ አለው። የራስን አከባቢ ማወቅን በሚመለከት የአከባቢውን ነዋሪ እውቀት የሚተካ ተራ ነጋዴ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም። በመሆኑም፤ የሐጎስ ዮሐንስ ግልብ ትንታኔ ነጭ አምላኪነትን እንዳያስከትል ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። የአፍሪቃ ቀንድ መሪዎችም ሆኑ መንግስታት እያንዳንዳችን በምንመለከትበት መነጽር ላያዩት ቢችሉም ጉዳያቸው ነውና ስለ አፍሪቃ ቀንድ በቂ ግንዛቤ እንደሚኖራቸው ጥያቄ ውስጥም ማስገባት የሚቻል አይደለም። ብዙ የተማሩና ስለ አከባቢው ጥናትና ምርምር የሚያካሂዱ ባለሙያ አማካሪዎችና ሌሎችም  እንደሚኖሩ መዘንጋት የለበትም። የሆነ ሆኖ ይህ ፀሐፊ አፍሪቃዊያን የራሳቸውን ጉዳይ ከማንም በላይ ራሳቸው ያውቁታል የሚል እምነት እንዳለው ግልጽ ማድረግ ይፈልጋል።

ቀጥሎ ደግሞ በሁለተኛ ፓረግራፍ ላይ፤

> ***“ እንደ አሜሪካ፤ ኤውሮጳ፤ ኤሲያ፤ ደቡብ አሜሪካ፤ ካናዳ…….ወዘተ ከመሳሰሉ የተለያዩ የዓለም አገሮች የመጡ ፕሮፌሰሮች ነበሩኝ። ይሁን እንጂ ስለአገሮቻቸውና መንግሥታቶቻቸው በአሉታ ሲናገሩ በፍጹም ሰምቼ አላውቅም።”*** *ይሉናል።*

በመጀመሪያ ደረጃ ማንኛውም የመንግሥት ተቀናቃኝ የሚከሰውና የሚያንኳስሰው የሚመለከተው አገር መንግሥትን እንጂ አገርን እንዳልሆነ ሐጎስ ዮሐንስ ልብ ሊሉት የሚገባ ጉዳይ ነበር። ይህ ማለት ግን አንዳንድ አጀንዳ አልባ ወይም በራስ መተማመን የሚጎድለው አለያም የቀወሰ ግለሰብ አይኖርም ለማለት አይደለም። በዓለማችን ላይ እንደነባራዊ ተደርጎ የተወሰደ እውነታ ግን ዜጎች የራሳቸውን መንግሥት መውቀስና ማንኳሰስ ብቻ ሳይሆን፤ መስፈርያው ሲሞላ በትጥቅም ጭምር በመፋለም መብታቸውን እንደሚያስከብሩ ነው። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በቱኒዚያ የተለኮሰው የለውጥ ነበልባል የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች አምባገነን መሪዎችን በመለብለብ ላይ እንደሆነ እያየነው ነው። “የተራበ ህዝብ መሪዎቹን ይበላል” አይደለ! ሪ/ፕሮፌ መረራ ጉዲና የሚሉት። በሰሜን አፊሪቃዊቷ ቱኒዚያ የተጀመረው መሪዎችን የሚበላ “አብዮት” ብዙ አገሮችን እያዳረሰ ነው፤ ገናም ማዳረሱ አይቀሬ ነገር ነው። እነዚህ አምባገነኖችን ለመፋለም የተነሳሱ ህዝቦች ከማንም በላይ አገራቸውን የሚወዱ ናቸው። መሪዎችን ግን ከመጥላት አልፈው እያሳደዷቸው መሆኑ እየታዘብነው ያለ ሃቅ ነው። ሐጎስ ዮሐንስ ፕሮፌሰሮቻቸው ስለ አገሮቻቸውና ስለ መንግስቶቻቸው መጥፎ ነገር ሲናገሩ ሰምተው አለማወቃቸውን ነግረውናል። ከላይ እንደተገለጸው፤ አገሩን የሚጠላ ፕሮፌሰርም ሆነ ተራ ዜጋ ይኖራል ብሎ ይህ ፀሐፊም አያምንም። አገርን አገር የሚያደርጉት በውስጡ የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው። አገር የሚለው ቃል ራሱ ከህዝብ ተለይቶ

ከተወሰደ ግዑዝ ነገር ነው። በመሆኑም ሊጠላም ሊወደድም አይችልም። አንድ ሰው አገሩን እንዲወድ የሚያስገድዱት ምክንያቶች እጅግ በርካታ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግልጽ ቢሆንም ከአስተዳደጉ ጋር በተያያዘ ካደገበት አከባቢና አገር ጋር የሚያስተሳስረው ሥነ-ልቦናዊ ቁርኝት እንዳለው መዘንጋት የለበትም። በመሆኑም አንድ ሰው ፕሮፌሰር እንበለው ተራ ዜጋ አገሩን የሚጠላበት ምክንያት ባለመኖሩ የሐጎስ ዮሐንስ ፕሮፌሰሮች ስለ አገሮቻቸው መጥፎ ነገር ሲናገሩ አለመስማት አዲስ ነገር አይሆንም። አዲስ ነገር የሚሆነው አገሮቻቸውን እንደሚጠሉ ቢገልጹ ነበር። ስለ መሪዎቻቸው መጥፎ ነገር አይናገሩም ያሉት ላይ ግን እንለያያለን። መሪዎች እንደ ማንም ዜጋ ሰዎች ናቸው። ሲያጠፉ ግን የሚያጠፉት ማንም ተራ ዜጋ እንደሚያደርሰው ዓይነት ተራ ጥፋት ብቻ አይደለም። በተለይ አምባገነን አገዛዞች አገርና ህዝብን የሚጎዱ አፍራሽ ወንጀሎችን ይፈጽማሉ። በዚህ ምክንያትም ከላይ እንደተገለጸው ህዝብ ስለነሱ መጥፎ ነገሮች ከመናገር አልፎ ይፋለማቸዋል። ይህ ደግሞ የዜጎች የማይገሰስ መብት ነው። አምባገነኖችን ልክ የሚያስገባ ህዝብ ደግሞ አገር ወዳድ ብቻ ሳይሆን ለትውልዶችም የሚያስብ የዜግነት ግዳጁን የሚወጣ ወገን ነው። ሐጎስ ዮሐንስ ራሳቸው በሚኖሩባት አሜሪካ የህዝብ ተወካዮችና የፌደሬሽን ምክርቤቶች አሉ። እነዚህ ምክርቤቶች በአብዛኛው ባገኙት የህዝብ ድምጽ መጠን በዴሞክራቶችና በረፓብሊካኖች ይያዛሉ። ታዲያ! በነዚህ ምክርቤቶች የሚታየው ፉክክር አንዱ ስለ ሌላው ወይንም ደግሞ ምክርቤቶቹ ስለ አስፈጻሚው አሉታዊ ነገሮች አይናገሩም ሊሉን ይሆን? ነው! ወይስ "ማጥላላት" ወይም "አሉታ" ለሚሉ አገላለፆች ያለን ትርጉም የተለያየ ነው? እስቲ ወደ ራሳችን እንመለስ? ሐጎስ የሐንስ 'ደርግ' መንግሥት አልነበረም ሊሉን ካልሆነ፣ ዛሬ እሳቸው የሚያመልኩት ሕወሓት ደርግን ከማጥላላትና ማውገዝ አልፎ በትጥቅ አልተፋለመውም ሊሉን ነው? ሕወሓት ደርግን ስያብጠለጥልባቸው የነበሩ "ታገል"፣ "ወይን" "People's Voice" የተባሉ የድርጅቱ ልሳኖች አልነበሩም እያሉን ይሆን? ክርክሩ የሚያዋጣ ክርክር አይደለም። ከላይ እንደተገለጸው ጤነኛ ዜጎች አገራቸውን አያንቋሽሹም አያወግዙምም። የሐጎስ ዮሐንስ ፕሮፌሰሮች ስለ መጥፎ መሪዎቻቸው መጥፎ ነገር የማይናገሩ ከሆነ የመሪዎቻቸውን መጥፎ ተግባር ስለሚጋሩ መሆን አለበት። ይህ ማለት በመጀመርያ ደረጃ ሰዎችን ደግ ወይም ጨካኝ መጥፎ የሚባሉት መሪዎች ስለሆኑ ሳይሆን ህዝብንና አገርን በሚመሩበት ጊዜ በሚፈጽሚቸው ወይም ባልፈጸሚቸው ተግባሮቻቸው መሆን አለበት። ስለሆነም የሐጎስ ዮሐንስ ፕሮፌሰሮች ተለቅመው በጎ ሥነ-ምግባርን ከሚከተሉ መሪዎች አገሮች የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ከሆነ ደግሞ በጎ፣ ላገርና ህዝብ የሚያስቡ መሪዎች ሊከበሩና ሊመሰገኑ ስለሚገባ፣ እነዚህ ሐጎስ ዮሐንስ የጠቀሷቸው ፕሮፌሰሮች ስለመሪዎቻቸው መጥፎ ነገር አለመናገራቸው ተገቢ ነው ብቻ ሳይሆን ሊተባበሩዋቸውና ሊያማክሯቸውም ይገባል። በሌላ በኩል ግን ስለ መጥፎ መሪዎቹ መጥፎ ነገር የማይናገር ፕሮፌሰር ጥሩና ጨዋ የሆነ ዜጋ ነው ለማለት ከሆነ አካሄዱ ትክክል አይሆንም። መረን የለቀቀ አድርባይነትና ራስ ወዳድነትም ሊሆን እንደሚችል ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው። ለዚህም እንደምሳሌ ለመጥቀስ ከተፈለገ "ጥልመት" የሚለውን የዶ/ር ሰሎሞን ዕንቋይና "Constitution for a Nation of Nations: The Ethiopian Prospect" የዶ/ር ፋሲል ናሆምን ሥራዎች ማንበብ ነው። እነዚህን መፃሕፍት አንብቦ በመሬት ላይ ከሚታየው እውነታ ጋር ያገናዘበ ሰው አድርባይነት ምን እንደሆነ ለመገንዘብ እንደሚችል የሚያጠራጥር አይደለም። ስለሆነም መንግሥትን ያመሰገነ ፕሮፌሰር ሁሉ ቅን ነው ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። የአንድ ሰው ቅንነትና ላገር ተቆርቋሪነት መለኪያ ስለ አንድ መንግሥት መጥፎ ወይም ደግ ነገር መናገሩ ሳይሆን፣ ስላለው ተጨባጭ እውነታ ምን ያህል በሙያ አንጻርና በቅን አመለካከት ይገመግመዋል የሚል መሆን ይገባል። በነገራችን ላይ ዶ/ር ፋሲል ናሆም ሁለቱን የደርግና የኢህአዴግ ሕገ-ምግሥታትን በማርቀቅ ላይ ተሳታፊ እንደነበሩ ልብ ሊባል ይ ገባል።

ቀጥለው አሁንም በሁለተኛ ፓረግራፍ ወደ መጨረሻ አከባቢ እንደሚከተለው ይላሉ፣ ሐጎስ ዮሐንስ

> **"ከማነኛውም ምንጭና በማነኛውም መልክ ከሚለገሰው እያንዳንዱ የውጭ ሰብአዊ እርዳታ በስተጀርባ ድብቅ ተልእኮ አለ!"**

ዋ!ሐጎስ ዮሐንስ! ይህ ነገር እነ አቶ መለስ ጆሮ እንዳይደርስ! ጉድ ይፈላል። እነ አቶ መለስ ራሳቸው ትግል ስጀምሩ ጀምሮ የሚኖሩት በእርዳታ ከተገኘው ገንዘብና ቁሳቁስ መሆኑ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው።ዛሬም ቢሆን የኢትዮጵያ ባጀት የሚነደፈው ከውጭ የሚገኘው እርዳታና ብድርን ታሳቢ በማድረግ ነው። ድሀ አገር ነንና ይህ በራሱ ምንም ወንጀል የለበትም። ይሁንና፤ "ድብቅ ተልእኮ" የሚለው ላይ ድብቅ የሚሆነው ከማን ነው የሚል ጥያቄን መጫሩ አይቀርም። እርዳታውን የሚቀበሉ መንግሥታት በአብዛኛው የሚሰጣቸው እርዳታም ሆነ የሚደረግላቸው ትብብር ምን ተልእኮ ለማስፈጸም እንደሆነ አስቀድመው የሚያውቁት ጉዳይ ነው። በሚደረግላቸው ትብብርም ሆነ በሚለገሳቸው እርዳታ ውስጥ በሰብአዊነት የሚደረግ የለም ተብሎ ሁሉም በአንድ ዘንቢል ውስጥ የሚጠቃለል ሊሆን የሚችል አይሆንም። ሆኖም በአብዛኛው የሚለገሰው እርዳታና ትብብር የራሱ የሆነ ተልእኮ እንዳለው ግልጽ እየታወቀ የሚመጣ እንጂ የተሰወረ ሚስጢር አይደለም። ይህ ደግሞ ዛሬ ዛሬ ዓለም በሙሉ የሚያውቀው ሐቅ እንጂ ተለይቶ ለሐጎስ ዮሐንስ የተገለጸ ነገር አይደለም። ለምሳሌ አሜሪካ ለኢትዮጵያ በምታደርገው እርዳታና ትብብር በስተጀርባ፤ ኢትዮጵያ አሜሪካ በአሸባሪዎች ላይ የምታካሂደውን ጦርነት እንድትደግፍ የሚያግባባ መሆኑ ግልጽ ነው። በሶማል የእስልምና አክራሪ ኃይሎች የመንግሥትን ሥልጣን ለመቆጣጠር በተቃረቡበት ወቅት፤ የኢትዮጵያ አገር መከላከያ ሠራዊት ሶማሊያ ውስጥ በመግባት ጦርነት ማካሄዱ የዚህ እርዳታና ትብብር አካል ተደርጎ የሚቆጠር ነው። ይህ ግን ድብቅ ተልእኮ ሳይሆን የኢትዮጵያ ገዢዎች አውቀውና ተቀብለው ያስፈጸሙት ተልእኮ ነው። የሆነ ሆኖ ሐጎስ ዮሐንስ ይህንን ከእርዳታ ጋር ተያይዞ የሚመጣን "ድብቅ ተልእኮ" ያሉት ነገር ከፃፉት ልበወለድ ጋር በምን መልኩ ሊያያይዙት እንደፈለጉ አሁንም ግልጽ ባይሆንም፤ ያነሱት አጀንዳ ነውና እግረ-መንገድ የተሰጠው አጭር አስተያየት በዚሁ ተቋጭቷል።

ሐጎስ ዮሐንስ በሁለተኛ ፓራግራፍ የመጨረሻ ዓረፍተ-ነገር ላይ እንደሚከተለው የሚል አስፍሯል፤

> **"አለመታደል ሆኖ ስለኛ ከራሳችን ኤክስፐርቶችና ባለሙያዎች ይበልጥ ሌሎች የውጭ ሰዎች የበለጠ ይረዳሉ፤ ያውቃሉ"**

መቼም ከህወሓት ጋር የተጠጋ የራሱ የሆነን ቁምነገር የመናቅና የማንኳሰስ ባሕሪ መላበሱ አይቀሬ ይመስላል። ህወሓት የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ ዓመት ታሪክ ነው ብሎ ከማመን አልፎ፤ ዛሬ ያንን ሊያሳምነን በመጣጣር ላይ ነው። ሐጎስ ዮሐንስም ከልክፍቱ አላመለጡም። ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ፤ የሚጽፉ ኢትዮጵያዊያን የታሪክ ጠበብቶች አሉን። ሁሉም የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪና ፀሐፊያን በእኩል ዓይን የምናያቸው ስሜታቸውን ሳይጨምሩ ታሪካዊ ሃቅን እንዳለ የሚያስቀምጡ ናቸው ብለን ለመመጻደቅ መሞከሩ አስፈላጊ ባይሆንም ድንቅ ተመራማሪዎች እንዳሉን ግን የሚካድ አይደለም። በኢኮኖሚው በኩልም ነብሳቸውን ይማርና እንደ ዶ/ር እሸቱ ጮሌ ያሉ እውቅ ኢኮኖሚስቶች ነበሩን አሁንም በሕይወት ያሉ የኢኮኖሚ ጠበብቶች አሉን። በሁሉም የሙያ ዘርፎች የተሟላ እውቀት ላይኖር ብችልም፤ ስለ ኢትዮጵያ ከማንም በላይ የሚያውቁ ኢትዮጵያዊያን ነበሩ! አሉም። በመሆኑም፤ ስለኛ የውጭ ዜጎች ከኛ የበለጠ ያውቃሉ የሚል እምነት መያዝ ነባራዊ ሃቅን መካድ ብቻ ሳይሆን ራስንም ማቅለል ነው። ለመሆኑ፤ ሐጎስ ዮሐንስና ተከታዮቻቸው ወዶ-ገብ ካድሬዎች የኢህአዴግ አምላኪ ሆነው ያ ሁሉ ኢህአዴግን በሙያው እያገለገለ ያለውን ኢትዮጵያዊ ምሁር ምንም የማያውቅ ዱንቆሮ ነው እያሉን መሆኑ ይገባቸው ይሆን?

ሐጎስ ዮሐንስ እ.ኤ.አ በ1995 ሮም ውስጥ አንዲት ወጣት ኤርትራዊት ንብረት በሆነው ቡናቤት ውስጥ አንድ ሰው ቡና ጋብዟቸው እንደሄዱ በመግለጽ የገጠማቸው ገጠመኝን እንደሚቀጥለው ያወሩናል።

> *“...... በቡናቤቱ ውስጥ ከመጠጥ መደርደርያው በላይ ባለው ግርግዳ ኤርትራ ተገንጥላ ይምትታይበት የኢትዮጵያና የኤርትራ ካርታ ተለጥፎ ነበር። አንድ በቢራ ስካር የደነዘዘ የሚመስል ኢትዮጵያዊ መጣና፣ ”ውድ ወዳጄ! እስቲ ካርታውን ተመልከተው! ይህ የኢትዮጵያ ካርታ ይመስላል? ይህንን ካርታ እንደ ኢትዮጵያ ካርታ ቆጥረን መቀበል ይኖርብናል?” ሲል ጠየቀኝ። “ጌታየ! ይህ አንተና እኔ ሮም ውስጥ እንደምናደርገው በቢራ ስካር የተገኘ ውጤት አይደለም! የሚልዮኖች ሕይወት ያስፈጀ፣ የዓመታት መራራ ትግል ውጤት ነው። ስለዚህ፣ ወደ ኢትዮጵያ ተራሮችና ጫካዎች ሂደህ ጥንት ወደ ነበረችበት መልሳት አልኩት።”*

ከዚህ አባባል ሐጎስ ዮሐንስም እንደ ህወሓት መሪዎች የኤርትራ መገንጠል አቀንቃኝ መሆናቸውን ነው። አመላለሳቸው ራሱ ከአቶ መለስ “መንገዱን ጨርቅ ያርግላቹህ” አነጋገር በምንም መልኩ የሚለይ አይደለም። ብዙ የህወሓት ካድሬዎች የሚታወቁት፣ የአቶ መለስን ቃላት ሳያላምጡ ውጠው በመድገም ነው። ሐጎስ ዮሐንስም የመዋጥና የመድገም ልክፍት አለማምለጣቸውን ለመገንዘብ ይቻላል። ከዚህ አባባላቸው ሐጎስ ዮሐንስ ለሻዓቢያ ያላቸው አድናቆትና ክብር ምን ያህል ጥልቀት እንዳለው ለመረዳት አይከብድም። *“ጌታየ! ይህ አንተና እኔ ሮም ውስጥ እንደምናደርገው በቢራ ስካር የተገኘ ውጤት አይደለም! የሚልዮኖች ሕይወት ያስፈጀ፣ የዓመታት መራራ ትግል ውጤት ነው።”* በማለት የመለሱት የሻዓቢያ ጥያቄ ተገቢና ሕጋዊ ነው ከሚል እምነታቸው የሚመነጭ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ፀሐፊ ደግሞ የሻዓቢያ ኤርትራን ማስገንጠል ሕጋዊም ሆነ ታሪካዊ መሠረት የለውም ብሎ ያምናል። ዛሬ ዛሬ! የሕወሓት መሪዎችና ካድሬዎችም፣ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ስለነበረች ነፃ ወጣች የሚለው ደማጎጂን ወደ ጎን ገሸሽ በማድረግ የሕገ-ምንግሥቱን አንቀጽ 39 ጋር አስታክከው “ ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፡ ብሔረሰብ፡ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው።” በሚለው መሠረት ነው የተገነጠሉት እያሉ ባሉበት ወቅት ሐጎስ ለሻዓቢያና ኢህአዴግ ኤርትራን የማስገንጠል አባዜ ዘብ ቆመው ይሟገታሉ። ይህ ነጥብ እዚህ ላይ የተነሳው ያለ ምክንያት አይደለም። የሐጎስ ዮሐንስ ፅሑፍ ከአንዱ ወደ ሌላው እየዘለለ አንዱን ከሌላው ጋር እያምታታ የሚሄድ በመሆኑ እዚህ ባነሱበት ቦታ ተነሳ እንጂ፣ ይህንን የተመለከተ ትንታኔ ከሚገጥምበት ርእስ ሥር ይቀርባል። ስለሆነም ሓሳቡን አትርሱብኝ፣ በቦታው እንመለስበታለን።

በሚቀጥለው ክፍል አምስት ላይ እስክንገናኝ መልካም ጊዜ!!!

ይቀጥላል …………………..

የካቲት 26 ቀን 2011 ዓ.ም.ፈ.